OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የYouth Arts 2025 መመሪያዎች

## የYouth Arts የስጦታ መረጃ

የYouth Arts ስጦታ በሲያትል ውስጥ ላሉ የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የበለጠ የሥነ-ጥበብ እና የባህል ዕድሎች እንዲኖሯቸው ለማድረግ የ2-ዓመት የሥነ-ጥበብ ፕሮግራምን ወጪ ይሸፍናል። እነዚህ ፕሮግራሞች የሚከናወኑት ከትምህርት ሰዓታት ውጭ ሲሆን የሚመሩትም በአርቲስት መምህራን ነው። ከተለያዩ የዘር እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዳራዎች ለመጡ ወጣቶች ከሥነ-ጥበበት ጋር እንዲላመዱ ተጨማሪ ዕድሎችን መፍጠር እንፈልጋለን።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት እያንዳንዱ ወጣት በዘሩ፣ በገቢው፣ በቤት ውስጥ በሚወራው ቋንቋ እና በልዩ የትምህርት ፍላጎቶች ምክንያት የሚያገኘው የሥነ-ጥበብ ትምህርት ዕድል ተመሳሳይ አይደለም። የሲያትል የሥነ-ጥበብ እና ባህል ቢሮ በCreative Youth Program አማካኝነት ፍትሃዊነትን ለማስጠበቅ በቁርጠኛነት ይሠራል።

እንደ ማመልከት፣ ብቁ መሆንዎን ማረጋገጥ ወይም የመስመር ላይ ሥርዓቱን መጠቀም ባሉ ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እርዳታ ካስፈለገዎት kristi.woo@seattle.gov ወይም 206-727-8671 ላይ የCreative Youth Development የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን ክሪስቲ ዉን ያነጋግሩ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪድዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ ሊያነጋግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** እርስዎ ብቻ ይደውሉልን እና የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ጥሪውን የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስከምናገኝ ድረስ ለአፍታ ይጠብቁን።

## ማመልከቻ

በሲያትል ከተማ የስጦታ ድረ ገጽ በኩል በመስመር ላይ ያመልክቱ፡-
https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new

በማመልከት ላይ ማናቸውም ዓይነት ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እገዛ ከፈለጉ፣ እባክዎ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጃችን የሆኑት ክሪስቲ ዉን 206-727-8671 ላይ በመደወል ወይም kristi.woo@seattle.gov ላይ ኢሜይል በማድረግ ያነጋግሯቸው።

**ለማመልከት የመጨረሻው ቀን ማክሰኞ፣ ማርች 4 2025፣ ከሰዓት 5 ሰዓት ላይ ነው። የፓሲፊክ ሰዓት።**
ከቀኑ 5:00 ሰዓት በኋላ የሚገቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## ብቁነት/መስፈርቶች

- ፕሮጀክቶችዎ በሴፕቴምበር 2025 – ኦገስት 2027 መካከል መደረግ አለባቸው። (የ2-ዓመት የጊዜ ገደብ)
- ብቁ አመልካቾች ግለሰብ አርቲስቶችን፣ መምህራን አርቲስቶችን፣ የሥነ-ጥበብ እና የባህል ድርጅቶችን፣ የወጣቶች አገልግሎት ኤጀንሲዎችን እና ኮሌጆችን ያካትታሉ።
- ፕሮግራሞችዎ ለመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚገኙ እና በሲያትል ከተማ ወሰን ውስጥ የሚከናወኑ መሆን አለባቸው። ጥያቄዎች ካሉዎት የፕሮጀክት ስራ አስኪያጃችንን ያነጋግሩ።
- መገኛ አድራሻዎ ከሲያትል ከተማ ወሰኖች ውጭ ሊሆን ይችላል።
- ሁሉም በተሸላሚዎች የሚቀጠሩ አርቲስቶች እና መምህራን አርቲስቶች ከመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና ከልዩ የጥበብ ፕሮጀክቶች ጋር በመሥራት ቢያንስ **የአንድ (1) ዓመት** ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።
- ፕሮጀክቶችዎ ከላይ እንደተገለፀው የYouth Arts ስጦታ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች የሚያንፀባርቁ እና ወጣቱን የማህበረሰብ ክፍል የሚደግፉ መሆን አለባቸው።

## የገንዘብ ድጋፍ

- ከተመረጡ፣ ለሁለት (2) ዓመታት ፕሮግራሞች የተከፋፈለ በድምሩ **$12,000** የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ፦ በ2025-2026 $6,000 እና በ2026-2027 $6,000።
- የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙት ፕሮግራሙ ከተጀመረ በኋላ ብቻ ነው። የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ ካስገቡ በኋላ ገንዘቡን በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ያገኛሉ። በክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝ ላይ ወደተገለጸው አድራሻ ቼክ በቀጥታ ይላካል። (ይህ አድራሻ በእርስዎ W9 ላይ ከተዘረዘረው አድራሻ ጋር መመሳሰል አለበት።) ምንም በአካል የማስገባት አማራጭ የለም።

ገንዘቦች ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፦

- የአርቲስት ክፍያዎች
- የወጣቶች ድጎማዎች
- የግብይት እና የማስተዋወቂያ ወጪዎች
- የፕሮጀክት አስተዳደር እና የሠራተኞች ወጪዎች
- አቅርቦቶች
- መሥሪያ ቦታ
- የመሣሪያ ኪራዮች
- ከፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ወጪዎች
- **አስቀድመው** በስጦታ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጃችን ፈቃድ ያገኙ ተጨማሪ ወጪዎች ሊፈቀዱ ይችላሉ

ገንዘቦች ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም፦

- የትምህርት ቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎች
- ገንዘቡ ከመሰጠቱ በፊት የተጠናቀቁት የታቀደው ፕሮጀክት ማናቸውም አካላት
- የመሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ግዢ
- የመሰባሰቢያ ዝግጅቶች ወይም ስጦታዎች

- የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ወይም ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች

ከተሸለሙ፣ የእኛ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ የከተማው ገንዘብ አጠቃቀም ከከተማው መመሪያዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## የመረጃ አውደ ጥናቶች

ስለዚህ ስጦታ እና እንዴት የእርስዎን ምርጥ ማመልከቻ ማስገባት እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ ይምጡ።

**የመረጃ ክፍለ ጊዜ 1**
ሐሙስ፣ ጃንዋሪ 30፣ 2025፣ 12 – 1 ከሰዓት።
[መልስ ይስጡ]

**የመረጃ ክፍለ ጊዜ 2**
ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 4፣ 2025፣ 5 - 6 ከሰዓት
[መልስ ይስጡ]

**የረቂቅ ግምገማ ክፍለ ጊዜ 1**
ረቡዕ፣ ፌብሩዋሪ 12፣ 5 – 6 ከሰዓት
[መልስ ይስጡ]

**የረቂቅ ግምገማ ክፍለ ጊዜ 2**
ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 18፣ 12 – 1 ከሰዓት
[መልስ ይስጡ]